# ምን ይሆን ጥፋቱ?!




(ለድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ-አፍሮ))



የኢትዮጵያችን ተስፋ ቡቃያው፣
ለመለመ ስንል አምሳያው፣
ጠላት ዳግም ዐይኑ ደም ለበሰ፤
አበባውን ሊቀጥፍ ተንቀሳቀሰ!

እኮ ምን ይሆን ጥፋቱ? አገር ምድሩ ተጨነቀ፤
መልሱስ ቀላል ነበር እውነታውን ላወቀ፤
ኢትዮጵያዊነት ነው አበሳው፤...
ጼጥሮሳዊነት ነው ግብሩ፤
ለሙሶሎኒ አሽከር ርዝራዥች...
ለባንዶች አለመገበሩ!

ግራም ነፈሰ-ቀኝ... «ወንጀል» «ኃጢዓት»... ቢደረደር፣
በሐሰት የፈጠራ ክስ - የቃለ-ዓቃቤው ዶሴ ቢከመር፣
ጥቁር ካባ የደረቡ - ሦስት ዳኞች ቢኮፈሱ፣
ወያኔያዊ ትያትር ነው - የህግ አንቀጽ ላይጠቅሱ፤
ቂም በቀል ነው መሠረቱ፤
በኢትዮጵያዊነት ላይ ነው ጥቃቱ::






ጀግኖች ያገር ልጆች ማወደሱ፣
የኢትዮጵያን ጠላት ማንኳሰሱ፣
«ሙሲሊም ክርስቲያኑን ማዋሃዱ»... «ኢትዮጵያዬ» ማለቱ፣
«በተስፋዋ ምድር እንዲፈጸም ቃሉ» መመኘቱ፣
«እውነት-እውነት እላችኋለሁ»... ማለቱ፣
ይሄ ነበርማ «ጥፋቱ»!

በፋሽስታዊ መተት ደንቃራ፣
በወያኔያዊ ስሌት ቀመራ፣
ኢትዮጵያዊነት ላይ የወረደ መዐት መከራ፣
ከአገር እስከ ግለ-ሰብ በተራ...፤
የቂም በቀል መወጫ፣
«ዳግም ትተነፍሱና..» መቀጣጫ...፣
ከግርግሩ በስተጀርባ - ከስለላው አውታር መቀመጫ፣
ይኸው ነው ምስጢሩ - የትያትሩ መቋጫ::





«ጊዜ የሰጠው ቅል...» ሆነና ነገሩ፣
በትዕቢት ተሞልተው አገር-ምድሩን ቢያስሩ፣
ጊዜው ሲደርስ ይፈረዳል!
ዕውነት ሃቅን ነፃ ያወጣል!!
«እስኪያልፍ ያለፋል» ነው ተረቱ፣
እስከዚያው አይለየን ብርታቱ!!

ጌታቸው አበራ
ሚያዚያ 2000 ዓ.ም
May 2008

(በድንቅ የፈጠራ ሥራዎቹ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ ተስፋን፣ አንድነትን፣ ታሪክን፣... እና ኢትዮጵያዊነትን ሲሰብክ ለነበረው ወጣት ድምፃዊ ለቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ-አፍሮ)፣ ለቤተሰቡና ለሙዚቃ አፍቃሪዎቹ ብርታትን እመኛለሁ::)